## ለ2020 ታንክስጊቪንግ ዴይ ኮንፍረንስ ቁልፍ መግለጫዎች

ለአንዱ አዲሱ ሰው ባሕላችንን በራሱ የሚተካው ክርስቶስ
ሁሉን-ያካተተው፣ ሁሉን-ደረስ የሆነው ክርስቶስ፣ ፊተኛ ስፍራ ያለው፣
የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ማዕከላዊነት እና አጽናፍ-ዓለማዊነት የሆነው [ክርስቶስ] ነው።

ሁሉን-ያካተተው፣ ሁሉን-ደረስ የሆነው ክርስቶስ ራእይ ሲኖረን፣
እርሱን እንደ ሕይወታችን እና እንደ መላው ማንነታችን ቅንብር ስንለማመደው
እና በባሕላችን ፈንታ እርሱን ስንኖረው፣ አንዱ አዲሱ ሰው ተግባራዊ በሆነ መንገድ
በመካከላችን ይገለጣል፣ የአዲሱንም ሰው ሕይወት እንገነዘባለን።

ባሕላችንን ለመተካት እና በእውነታ አንዱን አዲሱን ሰው ለመሆን
እንደ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም አዲስ በመሆን
በትንሣኤው ሕይወት ትኩስ አቅርቦት ዕለት በዕለት መታደስ ያስፈልገናል።

እውነታ በኢየሱስ እንዳለ ክርስቶስን በመማር
በባሕላችን ፈንታ የአንዱ አዲሱን ሰው ሕይወት መኖር ያስፈልገናል፤
ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ የኖረበት መንገድ
ዛሬ አንዱ አዲሱ ሰው ሊኖርበት የሚገባው መንገድ ነው።

*© 2020 Living Stream Ministry*

**ለታንክስጊቪንግ ኮንፍረንስ**
**መልእክቶች አውትላይኖች**
**ሕዳር 17-20፣ 2013**

**አጠቃላይ ርዕስ፡-**
**ሁሉን-ያካተተው፣ ሁሉን-ደረስየሆነው ክርስቶስ**
**ለአንዱ አዲሱ ሰው ባሕልን መተካቱ**

መልእክት አንድ

**የባሕላችን ሁሉን-ባካተተው፣ ሁሉን-ደረስ በሆነው**
**ክርስቶስ መተካት አስቸኳይ አስፈላጊነት**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፡- ቆላ. 1፡12-13፣ 15-18፣ 27፤ 2፡8፣ 14-15፤ 3፡4፣ 10-11

**I. የቆላስይስ መጽሐፍ የተጻፈው በቆላስይስ ያለችው ቤተ-ክርስቲያን በባሕል ተሞልታ ስለነበረና ቅዱሳን ከክርስቶስ በባሕል ተዘናግተው ስለነበረ ነው—2፡8፤ 16-17፤ 3፡10-11፡-**

ሀ. በቆላስይስ ባሕል ቤተ-ክርስቲያንን አጥለቅልቆ፣ ክርስቶስን ተክቶ እና ቅዱሳንን እንደምርኮ ወስዶ ነበር—2፡8።

ለ. የእግዚአብሔር ጠላት ክርስቶስን ለመተካት ባሕልን ይጠቀማል፤ ክርስቶስን ለመተካት የባሕልን መልካም ገጽታዎች ለመጠቀም ይሞክራል—ተዛ. ፊልጵ. 3፡4-8።

ሐ. በቆላስይስ መጽሐፍ መሠረት ክርስቶስ በባሕል ተተኪቷል፤ ቆላስይስ ለክርስቶስ ከፍተኛው ምትክ ባሕላችን እንደሆነ ያመለክታል።

መ. በቆላስይስ *የጨለማው ስልጣን* የሚያመለክተው በተለይም የባሕልንና የፍጥረታዊ ማንነታችንን መልካም ገጽታዎችን ነው—1፡12-13፡-

1. በቆላስይስ ያሉ ቅዱሳን ከፍተኛ የሆኑ የባሕል ገጽታዎች ቤተ-ክርስቲያንን እንዲወርሩ በመፍቀድ በጨለማ ስልጣን ስር ወድቀዋል—2፡8።
2. የባሕል ከፍተኛ ውጤቶች ሰይጣን ሰዎችን የሚቆጣጠርበት የጨለማ ስልጣን ገጽታዎች ናቸው—1፡13።
3. ለክርስቶስ ምትክ የሆነ ማንኛውም ነገር እኛን ለመቆጣጠር የጨለማ ስልጣን ይሆናል—ቁ. 13።

**II. የሰው ባሕል የተነሣው ከሰው ውድቀት በኋላ ነው—ዘፍ. 4፡16-22**

ሀ. ቃየን የእግዚአብሔርን መገኘት ትቶ ከሄደ በኋላ ለራሱ ጥበቃና በሕይወት መኖር ከተማን ሠራ—ቁ. 16-17፡-

1. በዚህ ከተማ ውስጥ ከእግዚአብሔር ውጭ የሆነ ባሕልን፣ እግዚአብሔር አልባ የሆነ ባሕልን አፈራ።
2. በገነት እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ ነገር—ከለላው፣ ጥበቃው፣ አቅርቦቱ እና መዝናኛው ነበር፤ ሰው እግዚአብሔርን ሲያጣ ሁሉን ነገር አጣ።
3. የሰው እግዚአብሔርን ማጣት ሰው የሰውን ባሕል እንዲፈጥር አስገደደው፤ የዚህም ነገር ዋና ዋና ንጥረ-ነገሮች ለመኖሪያ ከተሞች፣ ለኑሮ ከብት እርባታ፣ ለመደሰት ሙዚቃ እና ለመከላከል መሣሪያዎች ነበሩ—ቁ. 20-22።

ለ. እግዚአብሔር አልባ የሆነ ባሕል የተፈጠረው በእግዚአብሔር መንገድ ለመሄድ ፈቃደኛ ባልሆነ በዚህም እግዚአብሔርን ባጣ ሰው ይመስላል፤ በእውነቱ የባሕል መሠረታዊ ምክንያት ከእግዚአብሔር በተለየው ሰው ውስጥ የሰይጣን፣ የእግዚአብሔር ጠላት ማነሳሳት እና መገፋፋት ነበር—ቁ. 7፣ 16-17፤ ማቴ. 12፡26፡-

1. እንዲህ አይነቱ ከእግዚአብሔር ውጭ የሆነና ከሰይጣን ጋር አንድ የሆነ ባሕል፤ የዘመናት ሁሉ የሰው ባሕሎችን በሙሉ የሚወክል እና እነዚህ ባሕሎች ያለ እግዚአብሔር እንደ ሆኑ፣ ሰይጣንን እንደተከተሉ እና ከሰይጣን ጋር አንድ እንደሆኑ የሚያሳይ ሞዴል ሆነ—ተዛ. ሉቃ. 4፡6፤ የግርጌ ማስታወሻ 1(R.V.)።
2. እግዚአብሔር አልባ የሆነው ባሕል እንደ ዘር በዘፍጥረት 4 ተጀመረ፣ እናም በራእይ 18 በታላቂቷ ባቢሎን እስከሚጠናቀቅ ድረስ በሰው ዘር ታሪክ ሁሉ እየዳበረ ይሄዳል።
3. በማቴዎስ 24፡37-39 ያለው የጌታ ቃል በኖህ ዘመን የነበረው እግዚአብሔር አልባ ባሕል ጌታ በሚመጣበት ዘመን እስከመጨረሻው ደረጃ ደረስ የሚዳብር እንደሆነ ያመለክታል።

**III. ባሕል ስለ ክርስቶስ እና ቤተ-ክርስቲያን የሆነውን የእግዚአብሔርን አላማ የሚያስተጓጉል ነው—ኤፌ. 3፡10-11፤ 5፡32፡-**

ሀ. አንድ በጣም ስውርና ክፉ ነገር በክርስቶስና ቤተ-ክርስቲያን መንገድ ላይ ይቆማል፤ ይህ ስውር ተቃዋሚ ንጥረ-ነገር ባሕል ነው—ቆላ. 3፡10-11፤ ኤፌ. 2፡14-15፤ ቆላ 2፡14-15።

ለ. ባሕል ክርስቶስን እንዳንለማመድ ትልቅ እንቅፋት ነው። ሳናውቅ እና በተወሰነ መጠን አውቀን ክርስቶስን ከመለማመድ እና ከመደሰት በባሕል ተስተጓጉለናል—ፊልጵ. 3፡7-8።

ሐ. በሁሉ ነገር ወደ ክርስቶስ ማደጋችን እና ሙሉ ሰው ወደ መሆን መድረሳችን ስውርና አታላይ፣ ድብቅ በሆነው ባሕላችን ተደናቅፏል—ቆላ. 2፡19፤ ኤፌ. 4፡13፣ 15-16።

**IV. የሰው ልጅ ባሕል የእግዚአብሔርን መንግሥት በመቃወም ይቆማል—ማቴ. 10፡16-25፣ 34-39፤ 12፡29፣ 46-50፡-**

ሀ. የሰው ባሕል የሚቃወመውን ያህል ኃጢአተኛ ነገሮች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይቃወሙትም።

ለ. የሰው ባሕል የሰይጣን መንግሥት መሠረታዊ አካልና ታላቅ ክፍል ሆኗል—ቁ. 26።

ሐ. ባሕል የሰይጣን ምሽግ ሆኗል፤ ስውር እና አታላይ በሆነ መንገድ ባሕልን አጥብቆ ይይዛል የእግዚአብሔርንም መንግሥት ለመቃወም ይጠቀምበታል—ሐዋ. 26፡18፤ ቆላ. 1፡12-13።

**V. ክርስቶስ ሁሉን-እንዳካተተው፣ ሁሉን-ደረስ እንደሆነው ማንነት ከባሕል በተፃራሪ ነው እናም ባሕላችንን በራሱ መተካት አለበት—ቁ. 18፤ 3፡4፣ 10-11፡-**

ሀ. በቆላስይስ መጽሐፍ ያለው ሰፊ የሆነ የክርስቶስ መገለጥ አላማ ባሕልን ለማስወገድ ነው—2፡8፤ 3፡10-11።

ለ. በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ጳውሎስ ይህ ክርስቶስ ባሕላችንን መተካት እንዳለበት በሚለው ሀቅ እኛን ለመመሰጥ ሁሉን-ያካተተውን፣ ሁሉን-ደረስ የሆነውን ክርስቶስ ራእይ ያቀርባል—1፡27።

**VI. ባሕልን የሚተካው ክርስቶስ ሁሉን-ያካተተው፣ ሁሉን-ደረስ የሆነው ክርስቶስ፣ ፊተኛ ስፍራ ያለው፣ የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ማዕከላዊነትና አጽናፍ-ዓለማዊነት የሆነው [ክርስቶስ] ነው—ቁ. 15-18፤ 2፡16-17፤ 3፡4፣ 10-11፡-**

ሀ. ባሕላችንን መተካትና ለእኛ ሁሉን ነገር መሆን የሚችለው ክርስቶስ ሁሉን-ያካተተው፣ ሁሉን-ደረስ የሆነው ክርስቶስ ነው—1፡15፣ 18።

ለ. የቆላስይስ መጽሐፍ የተጻፈው ባሕላችንን የሚያስወግደውን እና ባሕላችንን በራሱ የሚተካውን ሁሉን-ያካተተውን፣ ሁሉን-ደረስ የሆነውን ክርስቶስ ለመግለጥ ነው—3፡4፣ 10-11።

ሐ. እግዚአብሔር በማዳኑ የሚያድነን ከኃጢአት፣ ከፍርድ፣ ከእሳት ባሕር፣ ዓለምና እኔነት ብቻ አይደለም፤ ባሕላችንን ጨምሮ ክርስቶስን ከሚተኩ ነገሮች ሁሉ ያድነናል—ዕብ. 7፡25።

መ. ሁሉን-ያካተተው፣ ሁሉን-ደረስ የሆነው ክርስቶስ በውስጣችን አለ፤ ሁለመናችንን እንዲሞላና ባሕላችንን በራሱ እንዲተካ ልንፈቅድለት ያስፈልጋል—ኤፌ. 3፡17፤ ቆላ. 1፡27፤ 3፡11።

*© 2020 Living Stream Ministry*